# ሱመያ አክሲዮን ማህበር

## ዉስን የሂሳብ መግለጫዎችና የኦዲተሮች ሪፖርት

## ሰኔ 30 ቀን 2015 ዓ/ል ለተጠናቀቀው የሂሳብ ዓመት

**ሱመያ አክሲዮን ማህበር**
**ሰኔ 30 ቀን 2015 ዓ/ል ለተጠናቀቀው የሂሳብ ዓመት**
**የተዘጋጀ የሂሳብ መግለጫ**

## ማውጫ ገጾች


| | |
|---|---|
| የገለልተኛ ኦዲተሮች ሪፖርት | 3-4 |
| የሂሳብ መግለጫዎች፡ | |
| የትርፍ ኪሳራ መግለጫ | 5 |
| የሀብትና ዕዳ መግለጫ | 6 |
| በባለአክሲዮኖች ሀብት ላይ የተከናወኑ ለውጦች መግለጫ | 7 |
| የገንዘብ ፍሰት መግለጫ | 8 |
| የሂሳብ መግለጫዎች ማጣቀሻዎች | 9-10 |

**_ሱመያ አክሲዮን ማህበር_**
**ሰኔ 30 ቀን 2014 ዓ.ም ለተጠናቀቀው የሂሳብ  አመት**
**በተዘጋጁት የአክሲዮን ማህበሩ የሂሣብ መግለጫዎች**
**ሳይ የቀረበ የውጭ ኦዲተሮች ሪፖርት**

**በተመረመረዉ የሂሳብ መግለጫዎች ሳይ የቀረበ ሪፖርት**

<u>የኦዲተሮች አስተያየት</u>

ከዚህ የኦዲት አስተያየት ጋር ከገፅ 5-10 በአባሪነት ተያይዘዉ የቀረቡትን ***ሱመያ*** አ/ማ የፋይናንስ ሪፖርቶች ማለትም ሰኔ 30 2014 የአክሲዮን ማህበሩን ሀብትና ዕዳ ሚዛን መግለጫ የትርፍ ኪሳራና ሌሎች አጠቃላይ ገቢዎች አመታዊ መግለጫ የባለአክሲዮኞች የሀብት ድርሻ አመታዊ እንቅስቃሴና ለዉጥ መግለጫ የኩባንያዉ የጥሬ ገንዘብ ፍሰት (እንቅስቃሴ) አመታዊ መግለጫና እንዲሁም የድርጅቱን ዋና ዋና ሂሳብ አያያዝ መርሆችና ሌሎች ተጨማሪ ማብራሪያዎችን መርምረናል፡፡

በኛ አስተያየት የተያያዙት ውሱን የሂሳብ መግለጫዎች ከመረመርናቸውና በአለም አቀፍ የሂሳብ አሰራርና ሪፖርት አቀራረብ ደንቦች /International Financial Reporting Standard/ እና በ2013 በወጣው የኢትዮጵያ ንግድ ህግ መሰረት በእንግሊዝኛ ቋንቋ ተዘጋጅተዉ ከቀረቡት የሂሳብ መግለጫዎች ተቀንጭበው የተወሰዱና የማይቃረኑ ናቸው፡፡

<u>ለኦዲተሩ (ሮች) አስተያየት መሰረቶች</u>

የኦዲት ስራችንን በአለምአቀፍ የኦዲት ደረጃ መሰረት አከናዉነናል፡፡ በዚህ የአለምአቀፍ የኦዲት ደረጃ መሰረት ያለብንን ሃላፊነት በሪፖርታችን ዉስጥ (የፋይናንስ ሪፖረቶችን ኦዲት በተመለከተ የኦዲተሮች ሃላፊነት) በሚል ርእስ ስር በዝርዝር አቅርበናል (ገልፀናል) ፡፡ እኛም በአለምአቀፍ የሂሳብ  ባለሙያዎች የስነምግባር ደረጃዎች ቦርድ  ደረጃና ከኦዲት ጋር ተያያዥነት ባላቸዉ የኢትዮጲያ ስነምግባር መመሪያዎች /ግዴታዎች መሰረት  ነፃና  ገለልተኛ ኦዲተሮች ስንሆን በኢትዮጲያ የኦዲት ስነምግባር ቦርድ የተጣሉብንን ሌሎች ስነምግባራዊ ሓላፊነቶች ተወጥተናል፡፡

<u>ሌሎች መረጃዎች</u>

በኢትዮጲያ የንግድ ህግ  ድንጋጌ መሰረት ተዘጋጅተው ከቀረቡት የሂሳብ መግለጫዎች ጋር ተካተው  የቀረቡት ሌሎች መረጃዎች የኩባንያው ዳይሬክተሮች ሃላፊነት ነዉ፡፡ በቀረቡት የሂሳብ መግለጫዎች ሳይ  የሰጠነው ሙያዊ አስተያየት እነዚህን ሌሎች መረጃዎች አያካትትም ፡፡

በፋይናንሻል ሪፖርቶች ሳይ  የቀረበዉ የኦዲተሮች አስትያየት ሌሎች መረጃዎችን የማያካትት ከመሆኑም በሳይ በእነዚህ ሳይ ምንም ዓይነት ማረጋገጫ አልሰጠንም፡፡ የፋይናሻል ሪፖርቶችን ኦዲት ማድረግን በተመለከተ የኦዲተሮች ሓላፊነት እነዚህ ተጨማሪ መረጃዎች ማንበብና ከቀረቡት የፋይናንስ ሪፖርቶችም ሆነ በኦዲት ስራችን አማካኝነት ካገኘነዉ መረጃ ጋር የማይጣረዙ መሆናቸዉን ወይም በጉልህ የተዛቡ  አለመሆናቸዉን ማየት መመርመርና ማረጋገጥ ነዉ፡፡

በኦዲት ስራችን ወቅት ያገኘናቸዉ የአዲት ማስረጃዎች ለሰጠነዉ አስተያየት በቂና አስተማማኝ ናቸዉ ብለን እናምናለን፡፡

<u>በፋይናንስ ሪፖርቶች ሳይ የዳይሬክተሮች ሃላፊነት</u>

በአለምአቀፍ የፋናንስ ሪፖርት አቀራረብ ደረጃና በኢትዮጲያ የ1952 ንግድ ህግ ድንጋጌ መሰረት የተዘጋጁና የኩባንያዉን አጥጋቢና ሚዛናዊ ገፅታ የሚያሳዩ የፋይናንስ ሪፖርቶችን የማቅረብና እንዲሁም ሚዛናዊ ገጽታቸዉን ከሚያዛቡ አበይት ግድፈቶች የማጭበርበር ተግባሮችና ስህተቶች ነፃ የሆኑ የፋይናንስ ሪፖርቶችን ለማዘጋጀች የሚያስችሉ የዉስጥ ቀጥጥር ስርአቶችን የመዘርጋትና ስራሳይ እንዲዉሉ ማድረግ የዳሬክተሮች  ሓላፊነት ነዉ፡፡

የፋይናንስ ሪፖርቶችን በተመለከተ የአክሲዮን ባለቤቶች ኩባንያዉን ለመዘጋትም ሆነ የንግድ ስራዉን ለማቋረጥ ሃሳብ ከሌላቸዉ ወይም ድርጅቱን ከማስቀጠል ዉጪ ሌላ ተጨባጭ አማራጭ ከሌላቸዉ ኩባንያዉን በንግድ ስራ ሳይ ሳልተወሰነ ጊዜ የመቀጠል አቅምን የመገምገምና ከዚህ ጋር ተያያዥነት ያላቸዉን ጉዳዮችም ሆነ የሂሳብ አያያዝ የድርጀት ቀጣይነት መርህን ተግባራዊነት የማሳወቅ ሃላፊነት የዳሬክተሮች ነዉ፡፡ ዳሬክተሮች የኩባንያዉን የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀት ሂደት የመቆጣጠር ሃላፊነት አለባቸዉ፡፡

<u>የፋይናንስ ሪፖርቶችን በተመለከተ የኦዲተሮች ሃላፊነት</u>

የኦዲተሮች ሃላፊነት ሪፖርቱን በወሳኝ መልኩ (Materially) ከሚያዛቡ አበይት ግድፈቶች ወይም የማጭበርበር ተግባራት ወይም የሂሳብ ስህተቶች ነፃ  ስለመሆናቸዉ በቂ ማስተማመኛ ማግኝትና በቀረቡት የፋይናንስ ሪፖርቶት ሳይ ገለልተኛ የሆነ ሙያዊ አስትያየት

መስጠት ነዉ። በቂ ማስተማመኛ ስንል ከፍተኛ ደረጃ ያለዉ ማስተማመኛ ማለት እንጂ በአለምአቀፍ የኦዲት ደረጃ መሰረት የተከናወነዉ ኦዲት ስራ የሂሳብ መግለጫዎች ላይ ሲኖር የሚችል ማናቸዉም መዛባትን ሁልጊዜ ሊያስገኝ የሚችል ዋስትና አይደለም። የፋይናንስ ሪፖርቶች መዛባት ከማጭበርበር ተግባራት ወይም ከሂሳብ አሰራር ስህተቶች የሚመነጭ ሲሆን የጎላ መዛባት ተብሎ የሚወሰደዉ እነዚህ መዛባቶች በተናጠልም ሆነ በጥቅል የፋይናንስ ሪፖረቶችን መሰረት በማድረግ በሚወሰድ የኢኮኖሚ ወሳኔዎች ላይ ተፅእኖ ማድረግ ሲችሉ ብቻ ነዉ።

የኦዲት ስራችን በአለምአቀፍ ኦዲት ደረጃ መሰረት በምናከናዉንበት ወቅት ሙያዊ ወሳኔ አሰጣጥን በተግባር ያዋልንና በምርመራ ሂደት ጊዜ ሲኖረን የሚገባንን ሙያዊ ስጋት (Professional skepticism) ተጠብቆ እንዲቆይ/እንዲዘልቅ አድርገናል።

በተጨማሪም

- በማጭበርበር ተግባራት ወይም በሂሳብ አሰራር ስህተቶች ሰደርሱ የሚችሉ አበይት የፋይናንስ ሪፖርቶች መዛባት አደጋዎችን የለየንና የገመገምን ሲሆን እነዚህን ስህተቶች ታሳቢ ያደረጉ የኦዲት አሰራር ስርአቶች (audit procedures) ቀርፅን ተግባራዊ ያደረግን ሲሆን ለኦዲት አስተያየታችን መሰረት የሆነ በቂና አስተማማኝ የኦዲት ማስረጃዎች አግኝተናል። የማጭበርበር ተግባራት የግለሰቦችን መመሳጠር ሆን ተብለዉ የሚደረጉ ግድፈቶችንና መዛባቶችን ወይም የዉስጥ ቁጥጥር ስርአት መጣስን የሚያካትቱ እንደመሆናቸዉ በስህተት ምክንያት ከሚደርሱ የሪፖርት መዛባቶች ይልቅ በማጭበርበር ምክንያት የሚመጡ ጉልህ የሪፖርት መዛባቶችን ያለማግኘት አደጋ ጣም ከፍተኛ ነዉ።
- ከተጨባጭ ሁኔታዉ ጋር የተገናዘበ የኦዲት ሂደት ለመቅረፅ የሚየስችለንን በቂ የዉስጥ ቁጥጥር ስርአት ግንዛቤ ያገኘን ሲሆን ይህ ግንዛቤያችን ግን የኩባንዉን የዉስጥ ቁጥጥር ስርአት ዉጤታማነት በተመለከተ አስተያየት ለመስጠት ሲባል የተከናወነ አይደለም።
- የኩባንያዉን የሂሳብ አያያዝ መርሆዎች ተገቢነት የሂሳብ ግምቶችን አሳማኝነትና ተንዳኝ የሆኑ የዳሬክተሮች መግለጫዎችን ተገቢነት ገምግመናል።
- በድርጅቱ የንግድ ስራ የማስቀጠል አቅም ዙሪያ ጉልህ የሆነ ጥርጣሬ ዉስጥ ሊያስገቡ የሚችሉ ክስተቶችና ሁኔታዎች ይኖሩ እንደሆነ ስንገመግም ባገኘነዉ የኦዲት ማስረጃ መሰረት ኩባንያዉ በንግድ ስራ ላይ ሳልተወሰነ ጊዜ የመቀጠል የሂሳብ አያያዝ መርህን መጠቀማቸዉ ተገቢ መሆኑን ደምድመናል። ይህንን በተመለከተ ጉልህ የሆነ አጠራጣሪ ጉዳይ ለስመኖሩ ድምዳሜ ላይ ብንደርስ ኖሮ ከዚህ ጋር ተያያዥነት ያላቸዉ ተጨማሪ መግለጫዎችን በኦዲት ሪፖርታችን በማካተት እንዲታወቁ እናደርግ እንደነበረ ወይም እነዚህ ተጨማሪ መግለጫዎች በቂ ሆነዉ ባይገኙ ኖሮ በኦዲት ሪፖርታችን በማካተት እንዲታወቁ እናደርግ እንደነበር ወይም እነዚህ ተጨማሪ መግለጫዎች በቂ ሆነዉ ባይገኙ ኖሮ በኦዲት ሪፖርታችን ላይ የሰጠነዉን አስተያየት ለማሻሻል (Modified opinion) እንገደድ ነበር። ድምዳሜዎቻችን የተመሰረቱት የኦዲት ሪፖርቱን እስከ አጠናቀቅንበት ቀን ደረስ ባገኘናቸዉ የኦዲት ማስረጃዎች መሰረት ነዉ። ሆኖም ከሪፖርታችን መጠናቀቅ በኋላ ሊደርስ ከሚችል ስህተቶችም ሆነ በሚፈጠሩ ሁኔዎች ምክንያት ኩባንያዉ የንግድ ስራዉን ሳልተወሰን ጊዜ ከማስቀጠል ሊገታ ይችላል።

- የፋይናንስ ሪፖርቶች አቀራረብ፣ አወቃቀርና ይዘት እንዲሁም ተጨማሪ መግለጫዎችንና የቀረቡት የፋይናንስ ሪፖርቶች መሰረታዊ የሆኑ የንግድ ልውውጦችንና ኩነቶችን ስለመወከላቸውና በሚዛናዊነት ስለመቅረባቸው አጠቃላይ የሆነ ግምገማ አካሂደናል።
- ከሌሎች ተንዳኝ ጉዳዮች በተጨማሪ ስለ ታቀደው የኦዲት ስራ ስፋትና ጊዜ ጉልህ የሆኑ የኦዲት ግኝቶችንና እንዲሁም በኦዲት ስራችን ወቅት ያገኘናቸውን ጎላ ያሉ የውስጥ ቁጥጥር ግድፈቶችና ድክመቶችን ለዳይሬክተሮች አቅርበናል።
- ያገኘናቸው የኦዲት ማስረጃዎች ላቀረብነው የኦዲት አስተያየት በቂና ተገቢ መሰረቶች ናቸው ብለን እናምናለን።

<u>ሌሎች ህግዊ ግዴታዎችን በተመለከተ የቀረቡ ሪፖርቶች</u>

ሀ) በኢትዮጲያ የንግድ ህግ 2013 በአንቀፅ 348 እና በ አንቀፅ 349 ድንጋጌ መሰረት በአነበብነዉ የዳሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት መነሻነት ለአክሲዮን ባለቤቶች ሲቀርብ የሚችል ምንም አይነት የተለየ ነገር አላገኘንም።

ለ) በኢትዮጲያ የንግድ ህግ 2013 አንቀጽ 349 መሰረት ተዘጋጅተው የቀረቡት የኩባንያዉ የፋይናንስ መግለጫዎች ባለአክሲዮኖቹ እንዲያፀድቁ ሓሳብ እናቀርባለን።

---

ሀሰን ሰይድ
የተፈቀደለት ኦዲተር
ትቅምት 29 ቀን 2016 ዓ.ል
አዲስአበባ